# ክፍለ ትምህርት አራት

## መሪዎች እቅድ ያወጣሉ፣ ያደራጃሉ

በሦስተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ የበርናባስንና የጳውሎስን እንደዚሁም የጢሞቴዎስን የመሪነት ምሳሌነት በመውሰድ ለመንፈሳዊ መሪነት ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎች ላይ በማተኮር ለመሪነት የተጠሩ ሰዎች እንደሚያድጉና ሌሎችን መንፈሳዊ አገልጋዮችና መሪዎችም እንዲያድጉ ለማድረግ የሚረዱበትን መንገድ ተገንዝበናል።

በዚህ በአራተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ ደግሞ የዳዊትን ምሳሌነት በመከተል የምናተኩረው ለመንፈሳዊ መሪነት ጠቃሚ የሚሆኑ መመሪያዎች ላይ ሲሆን፣ እቅድ ስለማውጣትና ስለ ማደራጀት ጠቃሚ የሆኑ ግንዛቤዎችን ለማግኘት እንሞክራለን።

**የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል**

- የዳዊት ምሳሌት
- መሪዎች ያቅዳሉ፣ ያስተባብራሉ
- መሪዎች ያደራጃሉ

------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች**

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- የዳዊት ሕይወትን መሠረት በማድረግ አንዳንድ የመሪነት መመሪያዎችን መግለጽና ተግባራዊ ማድረግ
- ድርጅት የሚለውን ሃሳብ መግለጽና ለድርጅታዊ አሠራር የሚረዱ አንዳንድ መመሪያዎችን ማስረዳት

----------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች**

1/ ስለ ዳዊት ሕይወት መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን በማንበብ ስለመሪነት ምሳሌ የሚሆኑ ባሕርያትን ተመልከት። ስለዚህም የሚረዱህ የመጽሐፍ ቅዱስ

የንባብ ክፍሎች 1ኛ ሳሙ 16፣1-22፣ 17፣21-58፣ ምዕራፍ 22-26፣ ምዕ 30፣ 2ኛ ሳሙ 5፡1-7፣ 7፡1-25 ፣ 1ኛ ዜና 17-19 እና 22-29 ናቸው። የአሁኑ ንባብ ዋና ዓላማ ዳዊት የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመፈጸም በእግዚአብሔር የተጠራ ሰው መሆኑን ለማመልከት ነው። የዳዊትን ሕይወት ምሳሌነት በጥንቃቄ ብትመረምር ስለመሪነት ብዙ መማር ትችላለህ።

2/ ትምህርቱን እንደሚገባ አጠናቅ፣ በተለመደው ሁኔታም ለቀረቡት ጥያቄዎች መልሰ ስጥ።

3/ በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ ያለውን የሙከራ ፈተና ውሰድ። መልሶችህን በመጽሐፉ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት የተሳሳትከውን ካለ አስተካክል።

**የክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ - የዳዊት ምሳሌነት**

**ዓላማ 1 ከዳዊት ድርጊቶች ውስጥ ቅዱሳት መጽሐፍት ስለ ችሎታ የሚሰጡትን ገለጻ ለመገንዘብ**

እስከ አሁን ድረስ የተመለከትነው የተለያዩ ሰዎች ምሳሌትን ነበር። ማለትም በመሪነት ላይ ስላሉ ሰዎችና አብረዋቸው ስለሚሠሩ ሰዎች። በዚህ ክፍለ ትምህርት ላይ ደግሞ ትኩረታችንን ከሰዎች ላይ አንሥተን ሥራው ላይና ሥራውን ለመሥራት በሚያስፈልገው ጉዳይ ላይ እናደርጋለን። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌያችን የሆነው ዳዊት ለአንድ መልካም መሪ የሚያስፈልጉትን ባሕሪያት ሁሉ የሚያሟላ መሪ ሲሆን፣ ስለዚህ ሰው በጣም የሚያስገርመው ነገር አስደናቂ ውጤቶችን ለማግኘት ያለው ብቃትና ችሎታ ነው።

ዳዊት የተለያዩ የሕይወት ልምምዶች አሉት። እረኛ፣ ወታደር፣ ባለቅኔ፣ አፍቃሪ አባትና ንጉሥ ነበር። ጀግና ነበር፣ በአንድ ወቅት በበደለኝነት ስሜት ቢሰቃይም፣ በደሉ ይቅር ተብሎለት እንደገና ተነሥቷል። የሕይወትን ውጣ ውረድ የምናየው ከዚህ ሰው ታሪክ ነው። የእግዚአብሔር እቅድ ምን ያህል ጥልቅና አስገራሚ እንደሆነም የሚያስረዳ ነው። ዳዊት ወደፊት ለሚጠብቀው ሥራ አስፈላጊው የሕይወት ተመክሮና እውቀት ተሰጥቶታል። የአካል ጥንካሬን፣ ድፍረትንና በራስ መተማመንን ያዳበረው በጎችን ሲጠብቅና ከማንኛውም አደጋ ሲከላከላቸው ነበር። ከበጎቹ ጋር ብቻውን በነበረበት ጊዜ ስለራሱ ለማሰብ በቂ ጊዜ

ነበረው፡፡ ነገሮችን ማሰላሰልና ሃሳቦቹንም ውብ በሆኑ ቃላት መግለጽንም ተምሯል፡፡

የሕይወት ጅማሬው በጣም ዝቅተኛ ቢሆንም፣ ለመሪነት የተጠራው ሳሙኤል በቀላልና ሊገባው በሚችል መንገድ ለንጉሥነት በመረጠው ጊዜ ነበር /1ኛ ሳሙ 16፡1-22/፡፡ ***"የእግዚአብሔር መንፈስ በዳዊት ላይ በኃይል ወረደ"*** በሁኔታው በልቡ እየተደነቀ ከተቀባ በኋላ ወደዚያው ወደ እረኝነቱ ተመለሰ፡፡ በኋላም በንጉሥ ሳኦል ቤተ መንግሥት ተራና ትሁት አገልጋይ ሆኖ አገለገለ፡፡

ሁሉም ፈርተውና ተርበትብተው በነበረበት ጊዜ ዳዊት ታላቁ ጎልያድን እንደሚገጥመውና እንደሚያሸንፈው በድፍረት መናገሩ ትህትናውን የሚያሳይ ድፍረት እንደሆነ ይታሰባል፡፡ ለዚህ ነበር ታላቅ ወንድሙ ዳዊትን **አንተኮ ትዕቢተኛ ነህ** በማለት የገሰጸው/1ኛ ሳሙ 17፡28-32/፡፡

ማንኛውም እውነተኛ መሪ ሊኖረው የሚገባውን ነገር ለማሳየት ግን ዳዊት ብዙም ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ ትህትናና አንድን ነገር ለማድረግ በወኔ መነሳሳት ለዳዊት ተቃራኒ አይደሉም፡፡ ዳዊት ጎልያድን በገደለበት ጊዜ እንደተረጋገጠውም ብዙውን ጊዜ ሁለቱ የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡

የሚሠራው ሁሉ በራሱ ጉልበት እንዳልሆነ ዳዊት ያውቃል፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወርዶበታል፣፡ ስለዚህም በድፍረትና በመተማመን መናገር ይችላል፡፡ ዳዊት በወኔ በተሞሉ ቃላት የሚኩራራ አልነበረም፡፡ እግዚአብሔር የሰጠውን ሥራ እንደሚገባ ማከናወን እንደሚችል ብቻ ነበር የተናገረው፡፡ ***"ከዚህ በፊት አንበሳና ድብ እንኳ ገድያለሁ"*** በማለት ተናግሯል ዳዊት /1ኛ ሳሙ 17፣ 34-37/፡፡

ያለምንም ወንጭፍና ድንጋይ እግዚአብሔር ጎልያድን መግደል እንደሚችል እናምናለን፡፡ ድንጋዩ በተአምር ተነስቶ ያለዳዊት ወይም ያለወንጭፍ እርዳታ ሊገድለው እንደሚችል እናውቃለን፡፡ ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር አንድ የሚሠራው ነገር ሲኖረው አስፈላጊውን ችሎታ ባዳበሩ ሰዎች እንደሚጠቀም ነው የምንመለከተው፡፡ ዳዊት ደግሞ ያንን ችሎታ አዳብሯል፡፡ ችሎታና ኃይሉን አሳይቷል፡፡ ምንም እንኳ ኃይሉ የእግዚአብሔር እንደሆነ ቢያውቅም ቸልተኛ ወይም ሞያ የሌለው ሰው አልነበረም፡፡ በረጅም ጊዜ ልምዱ የተማረውን ነበር ሥራ ላይ ያዋለው፡፡ ወንዝ ወርዶ

አስፈላጊ ድንጋዮች ሰበሰበ፡፡ በጥንቃቄ በእረኛ ኮሮጆው ውስጥ አኖራቸው እንጂ እንዲሁ የማይረቡ ድንጋዮችን እንዳልሰበሰበ ካሠራሩ ስልትና ሥርዓትን እንመለከታለን፡፡

ራሳችንን ለመገምገም የሚረዱን ጥያቄዎች ከማቅረባችን በፊት አስቀድመህ መዝ 144፡1 ላይ የተጻፈውን አንብብ፡፡ ዳዊት በራሱ ችሎታ ቢታመንም ክብሩን ለራሱ እንዳላደረገ ከዚህ ምንባብ ለመረዳት እንችላለን፡፡ ዳዊት እንዴት ነው ብቁ የሆነው? አንተስ ምን ዓይነት ችሎታ ወይም ስጦታ አለህ? እግዚአብሔር እጆችህን አሰልጥኗቸዋልን? ለጣቶችህስ እውቀት ሰጥቷቸዋልን? እነዚህ ያዳበርካቸው ችሎታዎችን አንድ ቀን ለጌታ ሥራ እንደምታውላቸው ታስባለህን?

## ዳዊት መሪያቸው ሆነ

በአስደናቂ ሁኔታ ድል ከተቀዳጀ በኃላ ዳዊት ክብርና ምሥጋናን አገኘ፡፡ ወዲያውኑ በሺህ የሚቆጠር ሠራዊት መሪ መሆን ይችል ነበር፡፡ ዳዊት ግን በአጋጣሚው በመጠቀም ዝነኛ መሆንን አልፈለገም፤፡ ይህም ትሕትናውን ነው የሚያሳየው፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ በፈቃደኝነት ለሳኦል ይታዘዝ ነበር፡፡ በመዋቅሩ ውስጥ ራሱን አስገባ፡፡ ልክ እንደ ወታደር ታዘዘ፡፡ በተደጋጋሚ ባስመዘገበው ድልና ባካበተውም ልምድ ምክንያት ዕድገትን አገኘ፡፡ ለሃገሪቱ ዕድገት በሚያስፈልጉ ሥራዎችና እንቅስቃሴዎች ይሳተፍ ነበር፡፡

1/ ዘወትር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈልግ ነበር፡፡

2/ ከበላዮቹም ሆነ ከእርሱ በታች ካሉት ጋር ባለው ግንኙነት ታማኝና ለሌሎችም አሳቢ ነበር፡፡

3/ ሁልጊዜ የተሻለና ብቃት ያለው ሆኖ ለመገኘት ይጥራል፡፣ ለዚህም ክብርን ለእግዚአብሔር ይሰጣል፡፡

ሁላችንም እንደምናውቀው በመጨረሻ ዳዊት ተስፋ የተገባለትን ሁሉ አግኝቷል፡፡ ይሁንና መላው እስራኤል ብቻ ሳይሆን፣ በአካባቢው ያሉ ጠላቶቹንም ገዝቷል፡፡ ይህም ብዙ ጊዜውን በጦርነት እንዲያሳልፍ ቢያደርገውም ድፍረትና ችሎታውን አዳብሮለታል፡፡

በንጉሥነት ሥልጣኑ ከተደላደለ በኂላ የዳዊት ትልቁ ፍላጎት ለቃል ኪዳኑ ታቦት ማረፊያ የሚሆን ቤተ መቅደስ መሥራት ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ማሟላት እንጂ ቤተ መቅደሱን መሥራት የእርሱ ድርሻ እንዳልሆነ ገለጸለት /1ኛ ዜና

22፡1-4/፡፡ ይህንንም ለማከናወን ያደረው እንቅስቃሴ የማደራጀትና የአሠራር መዋቅርን በመዘርጋት ረገድ ዓይነተኛ ምሳሌ ሆኗል፡፡

## ዳዊት ሰፊ ዝግጅት አደረገ

ዳዊት በረጅም ጊዜ የጦርነት ዘመኑ ብዙ ምርኮ አግኝቷል፡፡ ያገኘውንም ምርኮ ለእግዚአብሔር ቤት ግንባታ ቁሳቁሶችን ለማሟላት እንዳለበት አሰበ፡፡ /1ኛ ዜና 22፡1-14/፡፡ 1ኛና 2ኛ ዜና ስናነብ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር የነበረውን ግንኙነት በስፋት እንመለከታለን፡፡ የእነዚህ መጻሕፍት ዐቢይ መልእክት አምልኮ ወይም ታምራት ሳይሆን እቅድ ማውጣት፣ ማደራጀት፣ የሥራ ዝርዝር እና ለሥራው ገንዘብ ማሰባሰብ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡

ዳዊት ድንጋይ ጠራቢዎችንና ሌሎች ሠራተኞችን ቀጠረ፡፡ ለሥራው የሚያስፈልጋቸውን ድንጋይ፣ ብረት፣ ነሐስና ግንዶችን አቀረበላቸው ፡፡ የሥራው ተቆጣጣሪዎችን፣ ዳኞችን፣ ዘበኞችንና ሙዚቀኞችን አደራጀ፡፡ ለእያንዳንዳቸው ግልጽና የማያሻማ ሥራ ነበር የመደበላቸው፡፡ ቅድመ ዝግጅቶቹ ሁሉ ግልጽና ጥርት ያሉ መሆናቸው የብዙ ሥራና ጸሎት ውጤቶች መሆናቸውን ያሳያል፡፡

ዳዊት ልጁ ሰለሞንን፦ ***"የአምላክህን የእግዚአብሔርን ሕግ ትጠብቅ ዘንድ እግዚአብሔር ጥበብንና ማስተዋልን ይስጥህ--- ለእግዚአብሔር ቤት መቶ ሺህ መክሊት ብር፣ ሚዛንም የሌላቸውን ብዙ ናስና ብረት አዘጋጀሁ--- በአንተም ዘንድ ብዙ ሠራተኞች አሉ"*** አለው/1ኛ ዜና 22፡12-15/

ለቤተመቅደሱ ግንባታ፣ ዕቃ ቤት፣ ውስጠኛው ክፍልና የአደባባዮቹን እቅድ ሁሉ ሰጠው፡፡ ***"የእግዚአብሔር መንፈስ በልቡ እንዳስቀመጠለት"*** /1ኛ ዜና 28፡11-12/፡፡ ***"የሥራውን ሁሉ ምሳሌ አውቅ ዘንድ"*** አለ ዳዊት ***"በእግዚአብሔር እጅ ተጽፎ መጣልኝ"*** (1ኛ ዜና 28፡19)፡፡

ዳዊት የተለያየ የሕይወተ ልምምድ አለው፣፡ ብዙ ውጣ ውረድም አሳልፏል፡፡ በዚህ ሁሉ ግን በዓላማው ጽኑ ነበር፡፡ አልሞና አስተካክሎ በወነጨፈው ድንጋይ የጎልያድን ግንባር እንደመታ ሁሉ እቅዱ ያለምንም ስህተት ተፈጻሚነት እንዲኖረው ይጥር ነበር፡፡ ድካሙን ይቀበላል፡፣ ተጸጽቶም ንስሐ ይገባል፡፡ ጥበብና ማስተዋልን የሰጠው እግዚአብሔር መሆኑንና ለሌሎችም ጥበብና ማስተዋልን እንደሚሰጥ ያምናል፡፡

ጊዜው እያለፈ ሲሄድ ሥራውን ለሠራተኞቹ ኃላፊነቱንም ለሰለሞን የሚሰጥበት ወቅት መጣ። በኢየሩሳሌም ታላቅ ስብሰባ አድርጎ ለወደፊት ያለውን እቅድ ግልጽ አደረገላቸው። ምንም የዘነጋው ነገር አልነበረም። ምንም የሚያወላውልበት ነገር አልነበረም። የሚሠሩትን የሚያውቁ "ወንድሞች" በማለት ነበር ስለ ሠራተኞቹ የተናገረው። ሥራውን በተመለከተም እርስ በርስ ሊኖራቸው ስለሚገባው ግንኙነት ያውቃሉ። ለሥራው ስለሚያስፈልገው ነገርና የሚጠይቀውንም መስዋዕትነት ያውቃሉ። ራሱን ሳያስታብይ ዳዊት ለሥራው መረጃ ይሆናቸው ዘንድ ስሜቱንና ሥራውን ሁሉ ገለጸላቸው። ***"የአምላኬን ቤት ስለወደድሁ ለመቅደሱ ካዘጋጀሁት ሁሉ ሌላ የግል ገንዘቤን የሚሆን ወርቅና ብር አለኝና ለአምላኬ ቤት ሰጥቼዋለሁ"*** በማለት የማያወላውል ዓላማውን ነገራቸው (1ኛ ዜና 29፡3) ። ራሱን በሥራው በማሳተፉም ሌሎች ለማገልገልና ያላቸውንም እንዲሰጡ መልካም አርአያ ሆነላቸው። ሕዝቡ አመራሩን የተቀበሉት በታላቅ ደስታ ስለ ነበር ደስ እያላቸው ራሳቸውንና ያላቸውን ሁሉ ለጌታ ሰጡ።

ዳዊት ጸለየ፤ ሕዝቡንም በአምልኮ መራ። **እግዚአብሔር አምላካችሁን አመስግኑ** አለ በሕዝቡ ሁሉ ፊት። ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ (1ኛ ዜና 29፡10-20)። ወደ ትምህርቱ መጀመሪያ ሄደህ የዊሊያምና የኮሚቴውን ሁኔታ ተመልከት።

1/ ከዳዊት ምሳሌት በአመራር ስልት ልንከተላቸው የሚገቡን ቢያንስ ሦስት ነገሮችን ዘርዝር ።፡------------------------------

2/ የዳዊትን ምሳሌነት ባለመከተል የሚያስከትለውን ሦስት ነገሮች ዘርዝር ------------ - ------------------ -------------------

3/ ዳዊት ጎልያድን ለመዋጋት ያደረገውን ውሳኔ የሚያሳየው

ሀ/ ትዕቢተኛነቱን ለ/ ከሌሎች ልቆ ለመታየት መፈለጉን

ሐ/ ለመሪነት የተፈጠረ መሆኑን

መ/ እንደሚጠቀምበት በጌታ ያለው እምነት

4/ ዳዊት አንበሳና ድብ መግደሉን ሲገልጽ፡-

ሀ/ በሐቅ በተደገፈ ማስረጃ ነበር

ለ/ ከወንድሞቹ ይልቅ የእምነት ሰው መሆኑን ማሳየቱ ነበር

ሐ/ ለንጉሥነት መመረጡን መግለጹ ነበር

5/ ዳዊት በጥንቃቄ አምስት ድንጋዮችን መረጠ። ይህም የሚያመለክተው፡-

ሀ/ እምነት የሌለው መሆኑን ለ/ በቂ ልምድና ብቃት ያለው መሆኑን

ሐ/ ችሎታውን ለሕዝቡ ለማሳየት ያለውን ፍላጎት

መ/ በሳኦል መሣሪያ ለመጠቀም አለመፈለጉን

**መሪዎች ያቅዳሉ፣ ያስተባብራሉ**

**ዓላማ 2 ከእቅድ በስተጀርባ ያለውን ዓላማ ለመግለጽ**

እቅድ በጥንቃቄ ማሰብንና በጽሑፍ ማስፈርን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ ማንኛውም ውጤታማ ሊሆን የሚችል ሥራ በእነዚህ በሁለቱ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ በመጀመሪያ ማቀድ ከዚያም ማስተባበር ናቸው፡፡ አውቀውትም ይሁን ሳውቁት ሰዎች ሁሉ እቅድ ያቅዳሉ፡፡ አንድ ነገር እንዴት መሠራት ወይም ምን መምሰል እንዳለበት በአእምሮ የምንቀርጸው ምስል በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ሰብዓዊ ባሕርያት አንዱ ነው፡፡ የተለያዩ ሁኔታዎች ሲገጥሙን ምን እንደምናደርግ አስቀድመን እቅድ እናወጣለን፣ አስቀድመን ሥራውን በአእምሯችን እንሠራዋለን፡፡ በተለይም ለመሪነት የተጠሩ ሰዎች ይህን የሚያደርጉት ሌሎች ከሚያደርጉት ይልቅ ጥርት ባለና መልክ ባለው ሁኔታ ነው፡፡

ስለ መሪነት የተደረጉ ብዙ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት እቅድ ማውጣት በዝርዝር ጉዳዩች ውስጥ የመጀመሪያውን ሥፍራ ይይዛል፡፡ መሪዎች እቅድ ማውጣት አለባቸው፣፡ በጥንቃቄ እቅድ የማውጣታቸውን ያህል በዚያው ልክ ሥራውም ይከናወንላቸዋል፡፡ እስቲ አሁን ደግሞ እቅድ ማውጣት ስለሚያካትታቸው ጉዳዮች እንመልከት፡፡

**1/ ሁኔታዎችን መገምገምና መገመት፡-** መሪዎች የአሁኑን ሁኔታ በጥንቃቄ ያጠናሉ፡፡ ከአሁኑ ሁኔታ ተነስተውም የወደፊት ምን እንደሚመስል ወይም ምን መምሰል እንዳለበት ይገምታሉ፡፡

2/ **ዓላማና ግብ ያስቀምጣሉ፡-** መሪዎች ጥርት ያለ ሀሳብ ነው ያላቸው፡፡ ለሚሠሩት ሥራ ሁሉ ምክንያት አላቸው፡፡ የእያንዳንዱን ሥራ ዓላማ ያውቁታል፡፡ ውጤቱ ምን እንደሚሆንም ይረዱታል፡፡ እዚህ ላይ ውጤት የምንለው ነው፡፡ መልካም እቅድ ሁሉ ግብ አለው፡፡ ይህንንም ወደፊት በስፋት እንመለከተዋለን፡፡

3/ **ለሥራው ዝርዝር መመሪያን ማውጣት፡-** በመሪነት አሠራር ሂደት ውስጥ ይህ መርሐ ግብር ፕሮግራም ይባላል፡፡ የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት ግባችንንም ለመምታት ለምንወስደው እያንዳንዱ እርምጃ ሁሉ ዝርዝሮችን ያካትታል፡፡

4/ **የነገሮች ቅደም ተከተል፣-** የጊዜ ቅደም ተከተልን ማዘጋጀት ግብን ለመምታት ወይም በፕሮግራም መሠረት ለመንቀሳቀስ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ ተገቢውን የጊዜ ቅደም ተከተል ካልመደብንለት በቀር ማንኛውም ግብ ወይም ፕሮግራም ፍሬ አልባ ነው የሚሆነው፡፡

5/ **የሚያስፈልገውን ዘዴ ጥርት ባለ መንገድ መዘርዘር፡-** የምናወጣው እቅድ ተግባራዊና በሥራ ሊተረጎም የሚችል ዓይነት መሆን አለበት፡፡ ስለዚህም መሪዎች ማንኛውንም ነገር ለማከናወን የሚያስችላቸው ጥርት ያለ የአሠራር ዘዴ አላቸው፡፡

6/ **የገንዘብ አቅምን መተመን፡-** በመሪነት ጥናት ውስጥ ይህ በጀት መመደብ ይባላል፡፡ አብዛኞቹ እቅዶች ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ገንዘቡን ከየት እንደምናገኝ፣ የት እና ምን ላይ እንደምናውለው ጥናት ያስፈልገዋል፡፣ ይህን ለማድረግ ደግሞ ኃላፊነትን ለመውሰድ ፈቃደኛ መሆንን ይጨምራል፡፡

7/ **ለሥራው ብቁ የሚሆኑ ተገቢ ሰዎችን መምረጥ፡-** መሪዎች አንድ ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት ምን ያህል ሰዎች እንደሚያስፈልጉና ሰዎቹ ስላላቸው ችሎታና እውቀት ጥናት ያደርጋሉ፡፡ ለተገቢው ሥፍራ ተገቢ ሰዎችን መምረጥ እቅዳችንን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ በጣም ወሳኝነት አለው፡፡

8/ **የአሠራር ፖሊሲና መለኪያን ማዘጋጀት፡-** እያንዳንዱ እቅድ የራሱ ፖሊሲ አለው፡፡ እንዲህም ሲባል ክርስቲያኖች የሚመሩት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽንሰ ሃሳብና የቤተክርስቲያን ወይም የሌላ መንፈሳዊ ድርጅት የበላይ ባለሥልጣኖች በሚሰጣቸው መመሪያ ነው፡፡

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸውን ነጥቦች በጥያቄ መልክ መዘርዘር ብዙ መሪዎች ይበልጥ የሚረዳ ሆኖ አግኝተውታል፡፡ ለነዚህ ጥያቄዎች የምንሰጠው መልስ ለእቅድ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ያመለክተናል፡፡

1/ ለምንድነው ይህ ሥራ መሰራት ያለበት? አሁን ያለህበትን ሁኔታ

2/ ምንድነው ማከናወን ያለብኝ? ጥርት ያለ ግብ እንዲኖርህ ይረዳሃል

3/ እንዴት ነው መሠራት ያለበት? ዝርዝሮችን ለማውጣት ይረዳሃል፡፡

4/ መቼ ነው መሠራት ያለበት? ይህም ጊዜን ለመመደብ ይረዳሃል፡፡

5/ ሥራውን ለማከናወን የተሻለው መንገድ የትኛው ነው? ይህ የተለያዩ የአሠራር ዘዴዎችን እንድትመርጥና እንድታመዛዝን ይረዳሃል።

6/ በምንድነው ሥራውን ማከናወን የምንችለው? ይህ በጀት እንድትመድብና ለሥራው የሚያስፈልጉ ነገሮችን እንድታሰባስብ ይረዳሀል።

7/ ከነማን ወይም ከማን ጋር ነው የምሠራው? ይህ ሰዎችን እንድትመርጥና ለተገቢው ሥራ ተገቢው እውቀትና ችሎታ ያላቸውን ሰዎች እንድትመድብ ይረዳሀል።

8/ ለሠራተኞቹ ምን አይነት መመሪያ ወይም መመዘኛ ቢኖራቸው ይመረጣል?

## የተለያዩ የእቅድ ዓይነቶች

ብዙ መሪዎች በሦስት ዓይነት እቅዶች መጠቀምን ይመርጣሉ። እነርሱም፡-

1/ የዓመቱን እንቅስቃሴና የድርጅቱን አሠራር የሚያካትት እቅድ።

2/ የኮሚቴ ስብሰባ፣ የሠራተኞች ሥልጠና ፕሮግራምን የመሳሰሉትን የሚያካትት ዝርዝር የእንቅስቃሴ እቅድ።

3/ ኮንፍራንስ ወይም ልዩ ፕሮግራምን የሚያካትት የግል ፕሮጀክት

እቅድ ማውጣት በጥንቃቄ ማሰብንና በጽሑፍ ማስፈርን እንደሚጠይቅ ተመልክተናል። ይህ በጽሑፍ የሰፈረ እቅድ በሠነድ መልክ ይያዛል። ብዙ የተዋጣላቸው መሪዎች የረጅም ጊዜና የዕለታዊ ዝርዝር ጉዳዮች እቅድ ያወጣሉ።

## መደረግ ያለበት

1/ **እያንዳንዱ መሪ ለዕለታዊ ውሎው ዝርዝር እቅድ ያወጣል፡-** ይህንንም በማንኛውም ወረቀት ወይም ለዚሁ በተዘጋጀ ደብተር ላይ ማስፈር ይቻላል። የዕለታዊ ዝርዝር ጉዳዩች ፡- ቀጠሮን፣ መሠራት ያለበትን፣ ለሌሎች የሚሠጠውን ሥራ፣ መጻፍ ያለበት ደብዳቤን፣ መደረግ ያለበት የስልክ ጥሪ፣ ከማን የቴሌፎን ጥሪ እንደሚጠብቅ፣ የሚያስፈልጉ ነገሮችን፣ ገንዘብ-ነክና ሌሎች ጉዳዮች።

2/ **የቀን መቁጠሪያ፡-** ማንኛውም መሪ ሁለት የቀን መቁጠሪያ ያስፈልገዋል። አንደኛው ተለቅ ያለ ሲሆን፣ አንዳንድ ነገሮችን ለመጻፊያ ሥፍራ ሊኖረው ይገባል። ይህ ዓይነቱ የቀን መቁጠሪያ በረጅም ጊዜ እቅድ የሚውል ነው። ለዚሁ ተብለው የተዘጋጁ ካሌንደሮችን ማግኘት ካልተቻለ አመቺ በሆነ ሁኔታ ማዘጋጀት ይቻላል። በጣም አስፈላጊ የሆኑ ቀኖችን ማስታወስ እንዲቻል በትንሹ ካሌንደር ምልክት ይደረግበታል።

3/ **ማስታወሻ ደብተር፡-** ትንሹ ካሌንደር የደብተር ገጽ ወይም ደግሞ ሁልጊዜ በኪሳችን የምንይዘው ማስታወሻ ደብተር ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ትክክለኛ መሪ የዕለታዊ ውሎውንና ወደአእምሮው የሚመጣለትን ጠቃሚ ሃሳቦች በጽሑፍ ያሰፍራል፡፡ የሚፈልጋቸውን ሰዎች ስም፣ የቴሌፎን ቁጥርና አድራሻ ይጽፋል፡፡

4/ **የሥራ እቅድ ማስፈሪያ ወረቀት፡-** ዋና ዋና ጉዳዩችን አስመልክቶ የሚኖረን እቅድ በዝርዝር በጽሑፍ መስፈር ይኖርበታል፡፡ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- ቀን
- የመሪው ስም
- እቅዱን በማውጣት የተሳተፉ የሌሎች ሰዎች ወይም ኮሚቴ ስም
- የፕሮጀክቱ ስም፣ የሥራ ዝርዝርና ግቦች
- እያንዳንዱ ሰው የተሰጠው የሥራ ዓይነት
- ለእያንዳንዱ ሥራ የሚያስፈልጉ ነገሮች
- እያንዳንዱ ሥራ የሚጠናቀቅበት ቀን

5/ እቅድን ለማውጣት የሚያስፈልጉ ወይም የሚደረጉ ነገሮችን ዝርዝር እንደገና አንብብ፡፡ ከዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ምቹ በሆነ ሁኔታ የተቀመጠውን ፎርም አጥናው፡፡ ልክ አንድ ትልቅ እቅድ የማውጣት ኃላፊነት እንዳለብህ አድርገህ አስብ፡፡ ለዚሁ ተግባር የሚረዳህን ወረቀት በማዘጋጀት ወይም በተዘጋጀው በመጠቀም እቅድህን በትክክል አስፍር፡፡ ይህ በጣም የሚጠቅምህ ልምምድ ነው፡፡

## ማስተባበር

ማስተባበር ስንል እቅዱን በተግባር መተርጎም ማለታችን ነው፡፡ እቅዱን ካጠናቀቅህ በኋላ የሚቀጥለው ጉዳይ አስፈላጊውን ነገሮች ሁሉ በማመቻቸት ፍሬያማ በሆነ ሁኔታ ሥራ ላይ ማዋል ነው፡፡ ማስተባበር ትክክለኛ ሰዎች በትክክለኛው ጊዜ በትክክለኛው ሥፍራ መሆናቸውን፣ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ማሟላትንና እንዴት ሥራውን በጋራ መሥራት እንዳለባቸው እንዲረዱም ማድረግን ይጠይቃል፡፡

እንዴት እቅድ እንደምታወጣ እንዲረዱህ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንደገና ተመልከት፡፡ በጥያቄዎቹ ላይ የተዘረዘሩ ጉዳዮች ምንድናቸው?

6/ የሚከተሉትን አዛምድ፡- 1/ ጊዜ 2/ ሥራው 3/ ሰዎች

4/ ዘዴው 5/ አስፈላጊ ነገሮች 6/ ግቡ

-----ሀ/ ሥራውን የሚሰራው ማነው? ---መ/ ሥራው የሚሠራው መቼ ነው?

----ለ/ ሥራው የሚሰራው በምንድነው?------ሠ/ እንዴት ነው የሚሠራው?

---ሐ/ መከናወን ያለበት በምንድነው? ------- ረ/ ሥራው የሚሠራው የት ነው?

**ልናሰላስላቸው የሚገቡ ጥያቄዎች**

ስለዳዊት አመራር ታሪክ እንደገና ከመጽሐፍ ቅዱስ ተመልከት፡፡ መልካም አስተባባሪ ነበርን? እቅዶችን በሚገባ የሚያመዛዝን ነበርን? መቅደሱን ለመሥራት ከነበረው እቅድ ጋር በተያያዘ መልኩ ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ መስጠት ትችላለህ?

7/ ክሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ከእቅድ በስተጀርባ ያለውን ዓላማ በተሻለ ሁኔታ የሚገልጹት የትኞቹ ናቸው?

ሀ/ በመሠረቱ እቅድ ማውጣት ስንል የምናስበው ግብ ላይ መድረስ ነው

ለ/ የሥራ ሂደትን የተሳካ ለማድረግ የምናደርገው ሙከራ እቅድ ይባላል

ሐ/ የሥራ ሂደታችንን አስቀድሞ ለመወሰንና ወደግባችን ለመድረስም የምናደርገው ሙከራ የሚገጥሙን ሁኔታዎችን ሁሉ ለመወጣት ቅድመ ዝግጅት እቅድ ይባላል፡፡

መ/ እያንዳንድ ሰው መዋቅሩ ውስጥ የሚኖረውን ሥፍራና ያለበትንም ኃላፊነት የምንወስነው በእቅድ ነው፡፡

**አንዳንድ ችግሮችና መሰናክሎች**

**ዓላማ 3 በክርስቲያናዊ ሥራ ውስጥ ሊገጥሙን የሚችሉ ሦስት መሰናክሎችን ለመጥቀስ**

አንዳንድ ጊዜ መሪዎች "**ለሁሉም ነገር እቅድ አውጥቼ ነበር፣ ታዲያ ምን ዋጋ አለው?-----------**" ሲሉ ሰምተህ ይሆናል፡፡

"አብረውኝ ያሉ ሠራተኞች መመሪያ አይቀበሉም"

"አለቃዬ በየጊዜው ሀሳቡን ይለዋውጣል"

"ረዳቴ ታሟል"

"ሁኔታው ሁሉ እኔ ከጠበቅሁት በፍጹም የተለየ ነው"

ምናልባትም እንዲህ ያሉ ዓላማህን የሚያጨናግፉ ሁኔታዎች ገጥመውህ ይሆናል፣ ወይም ሊገጥሙህ ይችላሉ። በጥንቃቄ ያወጣኸውን እቅድ ሰዎች ላይቀበሉህ ይችላሉ። ስለዚያ ፕሮጀክት ምንም እቅድ ወይም ጥናት ያላደረገ ሌላው ሰው ሲዋጣለትና ሲከናወንለትም ታይ ይሆናል። ይህ ግን ምክንያት ሊሆንህ አይገባም። እቅድ ማውጣት ብቻውን መሳካትን ወይም መከናወንን እንደማያስገኝ ማወቅ አለብህ። አንዳንድ ሰዎች እቅድ ላለማውጣት ምክንያት አድርገው የሚያቀርቡት ይህንን ነው።

ልናስብባቸው የሚገቡን ሌሎች ሁለት እንቅፋቶችም አሉ። በክርስቲያናዊ ሥራ ውስጥ መሪዎች ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ይልቅ በእቅዳቸው ይታመናሉ ብለው ይከሷቸዋል። መንፈስ ቅዱስ የሥራችንን እንቅስቃሴ እንደሚመራ ሁሉ እቅድ ስናወጣም እንደሚመራን ከመጽሐፍ ቅዱስ ተመልክተናል። ስለዚህም እቅድ ማውጣትን ሆነ የሥራ መርሐ ግብርን የሚነቅፉ ሰዎች በቤተክርስቲያን መኖራቸው ብዙም ሊያስደንቀን አይገባም።

ምናልባትም ትክክለኛ እቅድን ለማውጣት ዋናው እንቅፋት የሚሆንብን ነገር ጊዜ የሚወስድና በርትተን መሥራትን የሚጠይቅ በመሆኑ ሊሆን ይችላል። በጥንቃቄ ማሰብና ሀሳብንም በጽሑፍ ማስፈር አስቸጋሪ ሥራዎች ናቸው። ምስክርነትህን በሕዝብ ፊት ቆመህ ከማሰማት በጽሑፍ ማስፈሩ ምን ያህል አዳጋች እንደሆነ አንተው ራስህ ልታየው ትችላለህ። ስንናገር ጌታ እንደሚመራን ሁሉ ስንጽፍም ሊመራን ይችላል። ስለዚህም በድንገት ስንናገር መንፈስ ቅዱስ እንደሚመራን የምናምን ከሆነ እቅዳችንን በጽሑፍ ስናሰፍር ግን አይመራንም ብሎ ማሰቡ ምክንያታዊ ሊሆን አይችልም፡ መሪው በሥራው ይበልጥ ፍሬያማ እንዲሆን ከተፈለገ እንደዚህ ያለው አለመግባባት ጨርሶ መወገድ አለበት። ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ጋር ጊዜን መስጠትና በርትቶ መስራት በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው።

8/ በመንፈሳዊ ሥራ ውስጥ ሊገጥሙን የሚችሉ ሦስት መሰናክሎችን ዘርዝር------------ ---------------- ------------------ ቀጥሎ አንዳንድ መሰናክሎችን ለማስወገድና ውጤታማ እቅዶችን እንድታወጣ የሚረዱ ሀሳቦች ቀርበዋል።

1/ እቅድህን ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት አሳልፈህ ስጥ፡- በጸሎትህ አስባቸው

2/ እንደ ሁኔታው አስፈላጊነት እቅዶችህን ለመለወጥ ዝግጁ ሁን፡- ዝርዝር እቅዶችን ማውጣትና እንደሁኔታው አስፈላጊነት እቅዶችን ለመለወጥ መዘጋጀት ብዙ ጊዜ መሪዎችን የሚገጥማቸው ችግር ነው።

3/ ሁሉም እቅዶች ተግባራዊ ይሆናሉ ብለህ አታስብ፡- አንድ መሪ ምንም እንኳ የመጀመሪያ እቅዱን መለወጥ ቢኖርበትም እቅዶችን ማውጣትና በእቅዱ መሠረትም መንቀሳቀስ ሥራውን ፍሬያማ እንደሚያደርግለት በሚገባ ያውቃል፡፡ ከብዙ ሁኔታዎች እንደሚታየው ምንም እንኳ ሁኔታዎች ቢለወጡም እንደሚገባ እቅድ ያደረገ መሪ የሌሎችን አክብሮትና ትብብር ያገኛል፡፡ የሚቻል ከሆነ ሊገጥሙህ የሚችሉ ችግሮችንም አስብባቸው፡፡ ሊደረጉ ይችላሉ የምትላቸውንም ለውጦች አስቀድመህ ለማሰብ ሞክር፡፡
4/ ትላልቅ ግቦች ላይ ለመድረስ ስለሚረዱ ትናንሽ ግቦች አስብ፡- ለምሳሌ ያህል በአጥቢያ ቤተክርስቲያንህ ለሚደረገው ኮንፍራንስ ምግብ ለማዘጋጀት ትልቁ እቅድህ ሊሆን ይችላል፡፣ ምግቡን የምታኖርበት ሥፍራና ለምግብ የሚሆኑ ነገሮችን ማግኘት ትንሹ እቅድህ ሊሆን ይችላል፡፡ ትንንሽ ግቦች ላይ ለመድረስ የምታደርገው እቅድ በከፍተኛው እቅድህ ላይ ይህን ያህል ጉዳት ሲያደርሱ ሊለወጡ ይችላሉ፡፡ ትናንሽና ትልልቅ ስለሚባሉት ዓላማዎች በሌላ ትምህርት እንነጋገርባቸዋለን፡፡
5/ በሥራው የሚሳተፉ ሰዎች ሁሉ እቅዶቹን እንደሚገባ መረዳታቸውን እርግጠኛ ሁን፡፡ ዳዊት ለሕዝቡ እንዴት እቅዶቹን እንደገለጸላቸውና ዓላማና ፈቃደኝነታቸውንም እንዲያሳዩ ዕድል እንደሰጣቸው አስተውል፡፡ የእቅዶችህን ዓላማና ጠቀሜታ አብረውህ ለሚሰሩ ሰዎች ግለጽላቸው፡፡ ለሚያደርጉት አስተዋጽኦም ምሥጋናህንና አድናቆትናን ግለጽላቸው፡፡ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ እቅዶችህን ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት በመስጠት አብረውህ በጸሎትና በምሥጋና እንዲሳተፉ አድርግ፡፡

*መሪዎች ያደራጃሉ*

## ግብ 4 የተለያዩ ድርጅታዊ ዓይነቶችን በመግለጽ ለድርጅታዊ አሠራር የሚጠቅሙ ነገሮችን ለማቅረብ

እቅድ ማውጣት ስንል የእቅዱን ሂደትና ለሥራው እንቅስቃሴ የሚረዳ የጽሑፍ ሠነድ ማዘጋጀትን እንደሚያካትት ተመልክተናል፡፡ ድርጅት የሚለው ሀሳብም እንዲሁ ሁለት ዋና ዋና ሀሳቦች የሚያካትት ሲሆን፣ በመጀመሪያ ለሥራው ብቃት ያላቸውን

ሰዎች ማሰባሰብ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ተደጋግፎ ለመሥራት የሚያስችላቸውን መዋቅርና አስተማማኝነት ያለው እቅድ መንደፍ ነው።

**የድርጅት ዓይነቶች**

ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆነን ወታደራዊ አደረጃጀት ነው። ዋናው መሪ ከፍተኛ ሥልጣን አለው። ሥራው የሚከናወነው በምክትሉና በመካከለኛው መሪዎች አማካይነት ነው። የእያንዳንዱ ሰው ሥራ ከእርሱ በላይ በሆነው ሹም ቁጥጥር ሥር ይሆናል። የሠራተኞቹ ግንኙነት ከቅርብ አለቆቻቸው ጋር እንጂ ከዋናው መሪ ጋር አይደለም።

ሌላው የአደረጃጀት ዓይነት አብዛኞቹ የዘመናችን ድርጅቶች የሚከተሉት ዓይነት ነው። አንድ ዋና መሪ ይኖራል። ምክርና መመሪያ የሚሰጡት እውቀቱና ችሎታው ያላቸው ሰዎች ይኖራሉ። ለዋናው መሪ ምክርና መመሪያ ይሰጡታል። እርሱም ለመካከለኛ መሪዎች ምክርና መመሪያ በመስጠት ሥራውን ያስፈጽማል።

ሦስተኛው የድርጅት ዓይነት የንግድ እንቅስቃሴን ወይም ካምፖኒን በተመለከተ እንደ ሥራው ዓይነት ተቀጣሪው ከተለያዩ የበላይ አለቆች ሥር በመሆን ሥራውን የሚያከናውንበት ነው። መሪዎቹም ጉዳይ ወይም ቀጥተኛ ግንኙነት ከሥራው ጋር እንጂ ከሰዎች ጋር አይደለም።

አብዛኛው ክርስቲያናዊ አሠራር ሦስቱን የአደረጃጀት ዓይነቶች ይጠቀሙባቸዋል። ዋናው መሪ መጋቢው ሲሆን፣ ረዳት መጋቢዎችም ሊኖሩት ይችላሉ። የእሁድ ትምህርት ቤትና የመዘምራን ክፍል ኃላፊዎችን የመሳሰሉ መካከለኛ መሪዎችም ሊኖሩት ይችላሉ። የመዘምራኑ ቡድን በቡድን መሪ ሥር ሲሆን፣ የቡድኑ መሪ ደግሞ ከረዳት መጋቢው ሥር ይሆናል። ቤተክርስቲያን እንዲህ ያለውን የአሠራር ዘዴ የምትጠቀምበት በመጠኑ ነው። ብዙውን ጊዜ እንደምናየው መሪዎቹ ሁሉ ከመጋቢው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው። ስለዚህም አሠራሩ የቡድን አደረጃጀት መሥመር ዓይነት ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ሥራዎች እንደመኖራቸው መጠን በሥራው አማካኝነት መሪዎቹ ሁሉ እርስ በርስ ይገናኛሉ።

የተለያዩ ሥራዎችና እንቅስቃሴዎች ስላሉ መጋቢው ከሰዎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ውስብስብና ባለብዙ መልክ ነው። መጋቢው የማሕበረ ምዕመኑ መንፈሳዊ መሪ ነው። በድርጅታዊ መዋቅሩ ውስጥ ዋና መሪ እንደ መሆኑ መጠን ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ባለው ግንኙነት የበላይ ነው። ለምዕመኑ የምክር አገልግሎት መስጠትና

ማስተማርም የእርሱ ኃላፊነት ነው፡፡ ፍሬያማ የሆነ ድርጅታዊ እንቅስቃሴ እንዲኖረን ከተፈለገ የመጋቢውን የተለያየ የሥራ ድርሻ ልንረዳለት ይገባል፡፡

መንፈሳዊ መሪ አስተማሪና ምክር ሰጪ እንደመሆኑ መጠን መጋቢው ከእያንዳንዱ ምዕመን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ዋና መሪነቱና አስተዳዳሪነቱ ግን ኃላፊነትንና ሥልጣንን ካካፈላቸው ከሌሎች መሪዎች ጋር መሥራት ይኖርበታል፡፡ እንዲህ ያለው የሕብረት አሠራር የቤተክርስቲያኑን ሥራ ፍሬያማ ያደርገዋል፡፡ በዚህ መልክ መደራጀቱ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ለሁሉም ወገኖች ሥራውን ቀላል ያደርገዋል፡፡ ረዳቶቹ ሥራውን እንደሚወጡ መጋቢው በረዳቶቹ ላይ ሙሉ እምነት ይኖረዋል፡፡ መካከለኛው መሪ ከቡድኑ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ይበልጥ ፍሬያማ ይሆናል፡፡ በመዋቅሩ ውስጥ የሚኖራቸውን ሥፍራና ጥያቄ፣ ሲኖራቸውም ምን እንደሚያደርጉ ስለሚያውቁ ሠራተኞቹ በራስ የመተማመን ስሜት ይኖራቸዋል፡፡

## መሪውና ድርጅቱ

### ዓላማ 5 መሪው ከድርጅቱ ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ለመግለጽ

ብዙ መሪዎች ከድርጅቱ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በሁለት መንገድ ነው፡፡ በመጀመሪያ በድርጅቱ ውስጥ ያላቸውን ትክክለኛ ሥፍራ ያውቃሉ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በራሳቸው ኃላፊነት ዙሪያ እንዴት እንደሚያደራጁ ሊያውቁ ይገባል፡፡ አስቀድመን እንደተመለከትነው ውጤታማ የአመራር ስልት በራሱ በመሪው ጥረትና የሚሠራበት መዋቅር ውጤት ነው፡፡ ደካማ አመራር ያለው ጠንካራ ድርጅት መዋቅር አልባ ሊሆን ይችላል፡፡ ደካማ ድርጅታዊ መዋቅር ውስጥ ያለ መልካም መሪም እንዲሁ ውጤት አልባ ሊሆን ይችላል፡፡ በመንፈሳዊ ሥራ፣ ሥራውን በሚገባ ለማከናወንና ዓላማን እግቡ ለማድረስ ሁለቱም ያስፈልጋሉ፡፡

ስለዚህም የመሪነት ሥልጣን ስትቀበል መዋቅሩን እንደሚገባ መረዳት አለብህ ማለት ነው፡፡ የድርጅቱን አስተዳደር ሰንጠረዥ አጥናው፡፡ የሥራ ድርሻህን እንዲያብራሩልህ የበላዮችህን ጠይቃቸው፡፡ የሚጠበቅብህን እወቅ፡፡ ምናልባትም በጽሑፍ የሠፈረ የሥራ ዝርዝር ሊሰጥህ ይችላል፡ አንተም ሆንህ ሌሎች ጥርት ያለ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ነው የሚፈለገው፡፡ ሌሎችን በበላይነት እንድትመራ ከተፈለገም፣ የሥራ ድርሻህን ለሌሎች ለማሳወቅ ስብሰባ መጥራት ሊያስፈልግህ ይችላል፡፡

እንዴት እንደምታደራጅ

አዲስ ድርጅትን እንድታዋቅር ወይም ቀድሞ የነበረውን እንድታሻሽል ከተፈለገ ከፍተኛ ኃላፊነት ተጥሎብሀል ማለት ነው፡፡ ቀጥሎ መመሪያ ሊሆኑህ የሚችሉ አንዳንድ ነጥቦች ተሰጥተዋል፡-

1/ የሥራ ዝርዝሮችን ወይም ደግሞ ግላማዎቹን እግብ ለመድረስ መደረግ ያለበትን የሥራ ዝርዝር አውጣ፡፡

2/ ለሥራው መሳካት ምን ያህል ሰዎች እንደሚያስፈልጉህ በማጥናት የእያንዳንዱን ሰው የሥራ ድርሻ ዘርዝር ፡፡

3/ የአንዱ የሥራ ድርሻ ከሌሎች የሥራ ድርሻ ጋር ያለውን ግንኙነት አንተም ሆንህ ሌሎች በደንብ እንድትረዱት ሠንጠረዥ አውጣ፡፡

4/ ተገቢ ሰዎችን በተገቢው ሥፍራ አድርግ፡፡ (ትክክለኛ ሰዎችን እስክታገኝ ድረስ የፈጀ ጊዜ ቢፈጅ ኃላፊነት በሚጠይቅ ሥፍራ ላይ ማንንም አታስቀምጥ፡፡ ከዚህ ይልቅ ተገቢውን ሰው ፈልገህ አሰልጥን፡፡

5/ በተቻለ መጠን አብረውህ ለሚሰሩ ሰዎች አስፈላጊውን መረጃ ስጣቸው፡፡ አንድ ጊዜ ለሁሉም ገለጻ ከሰጠህ በኃላ ግር ያላቸውን ነገር እንዲጠይቁ እድል ስጣቸው፡፡

6/ እያንዳንዱ ሰው ያለበትን ኃላፊነት (ተጠያቂነት) በግልጽ አስቀምጥ፡፡ እያንዳንዱ ሠራተኛ የሚጠበቅበትን፣ መብትና ግዴታውን ምን ድረስ እንደሆነ ይወቅ፡፡ እቅድ ለማውጣት በሚጠቅሙ ማለትም መቼ? የት? እንዴት? በሚሉ ጥያቄዎች ተጠቀም፡፡ የሥራ ውጤታቸውን እንዴት በጽሑፍ እንደሚያሰፍሩና እንዴት ሪፖርት እንደሚያቀርቡ አስተምራቸው፡፡ ሥራው የሚጠናቀቅበትን ጊዜ ወሰን፣ የድርጅቱን አሠራር ፖሊሲ አብራራላቸው፡፡ አንተም ሆንህ ሌሎች ከተመክሯቸው እንዲማሩና ለወደፊቱም መሻሻል እንዲያደርጉ ሥራውን የምትገምተው፣ ውጤቱንም የምትመዝኑበት ዘዴ ይኑራችሁ፡፡

10/ ከድርጅቱ ጋር በሚኖረው ግንኙነት መሪው፡-

ሀ/ በድርጅቱ ውስጥ ያለውን ሥፍራ ማወቅ አለበት

ለ/ የሚጠበቅበትን ማወቅ አለበት፡፡

ሐ/ በመዋቅሩ ውስጥ ያለውን ሥፍራ ማወቅ አለበት፡፡

መ/ የሥልጣኑ ገደብ ምን ያህል መሆኑን ማወቅ አለበት፡፡

**የሙከራ ፈተና**

**እውነት ወይም ሐሰት፡- በእያንዳንዱ እውነት በሆነው ዐረፍተ ነገር ፊት ባለው ክፍት ቦታ "እ"፡ ሐሰት በሆነው ዐረፍተ ነገር "ሐ" ፊደልን በመጻፍ በተሰጠው ቦታ መልስህን አስፍር፡፡**

-----1/ ከዳዊት ሕይወት እንደምንመለከተው ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ጥሪ የሚመጣለት በተፈጥሯዊ ችሎታው አስቀድሞ መጠቀም ሲችል ነው፡፡

----2/ ትህትናና ድፍረት አስፈላጊ ባሕርያት ናቸው፡፡ ደፋሮች የምንሆነው እግዚእብሔር የብርታታችን ምንጭ መሆኑን ስለምናውቅ ነው፡፡ የትህትናችን መሠረት ደግሞ ክብሩ ሁሉ የእግዚአብሔር መሆኑን ስለምናውቅ ነው፡፡

------- 3/ ዳዊት በጎልያድ ላይ የተቀዳጀው ታላቅ ድል መሪ አድርጎታል፡፡ ስለዚህም የራሱን ፈቃድ ለማሟላት ነጻ ነበር፡፡

------- 4/ ከዳዊት ህይወት የምንመለከታቸው ሶስት የአመራር ዘዴዎች፡-

1/ ዘወትር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈልግ ነበር፡፡

2/ ከበላዮቹም ሆነ ከበታቾቹ ጋር በነበረው ግንኙነት ፍጹም ታማኝ ነበር፡፡

3/ ክብርን ለእግዚአብሔር እየሰጠ ምንጊዜም የተሻለና ብቁ ሆኖ ለመገኘት ይጥር ነበር፡፡

---5/ ምንም እንኳ ዳዊት ቤተመቅደስን ለመሥራት ባይፈቀድለትም ለቤተመቅደሱ ግንባታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ማሟላት ነበረበት፡፡ ይህ የሥራ ክፍፍል ዳዊት የመገንባት ብቃት እንዳልነበረው ነው የሚያመለክተው፡፡

--- 6/ እቅድ ማውጣት በሃሳባችን የምናደርገው ቢሆንም አስፈላጊው ነገር ማሰቡ ሳይሆን በተግባር መፈጸሙ ላይ ነው፡፡

----7/ ዳዊት ካደረገው ዝግጅት የምንመለከተው ምሳሌ በሥራ ክፍፍል ከብዙ መሪዎች አንዱ መሆኑን ነው፡ አንዱ ያዘጋጃል፡፡ ሌላው ይሠራል፡፡ ይሁን እንጂ ሥራውን ተፈጻሚ የሚያደርግ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

----8/ መቅደሱን ለመገንባት ካደረገው ዝግጅት መልካም የአመራር ባሕርያትን እንመለከታለን፡፡ እቅድ ነበረው፡፡ ለሠራተኞቹ አስፈላጊውን መመሪያ ይሰጥ ነበር፣፡ ለመቅደሱ ሥራ አስፈላጊውን ሁሉ አሟልቷል፡፡

------9/ ያለበቂ እቅድ የሚደረጉ ነገሮች ብቻ ናቸው ሁለቱ መሠራት ያለባቸው፡፡

-------10/ እቅድ ጊዜን፣ ጉልበትንና ገንዘብን ይጠይቃል፡፡ ስለዚህም አስፈላጊ የሚሆነው ወጪንና የብዙ ሰዎችን ተሳትፎ በሚጠይቅ ሥራ ብቻ ነው፡፡

-----11/ በመሠረቱ እቅድ የአእምሮ ሥራ ብቻ ነው፡፡

------12/ እቅድ ማውጣት ለሥራው መሳካት ዋስትና ነው፡፡

------13/ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች **ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ይልቅ የተደገፍከው ፕሮግራምህን ነው** በማለት መሪውን ሲወቅሱ ይሰማል፡፡ ስለዚህም በመንፈሳዊ ሥራ ውስጥ “ዕቅድ” ማውጣት እንቅፋት እንደሆነ ይታሰባል፡፡

-----14/ እግዚአብሔር ሥራችንን እንደሚባርክ ሁሉ እቅዳችንንም መባረክ እንደሚችል ቅዱሳት መጻሕፍት ያሳያሉ፡፡

-----15/ እንደ ሁኔታው አስፈላጊነት እንዲለወጡ ሆነው የተዘጋጁ ይሆናሉ፡፡

------16/ ድርጅት ሰዎች እርስ በርሳቸው እንዴት ግንኙኘነት ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው በሚያሳይ እቅድ ላይ ውጤታማ ለሆነ ሥራ የግንኙነት መስመር መዘርጋት ነው፡፡

------17/ የሕዝቡ ፍላጎት እንዲሟላ መሪውም እንዲከበር ከተፈለገ የድርጅቱ የሥልጣን መስመር መከበር ይኖርበታል፡፡

------18/ በዋናው መሪና በሌሎች መሪዎች መካከል አለመግባባት እንዳይኖር በየግዜው ተገናኝተው መወያየት አለባቸው፡፡

-----19/ በመካከለኛው መሪ ሥር ያለ ግለሰብ ወደ ዋናው መሪ ቢሄድ ዋናው መሪ መካከለኛውን መሪ ሳያሳትፍ ለጉዳዩ እልባት ሊሰጥ ይችላል፡፡

----20/ ክርስቲያናዊ አገልግሎት እንደሚገባ እንዲሠራ ከተፈለገ መልካም ድርጅትና መልካም አመራር ሊኖር ይገባል፡፡

**የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች**

1/ መልስህ ሊሆኑ የሚችሉ፡- ለእግዚአብሔር ሥራ እቅድ ነበረው፡፡ ሰዎች ራሳቸውን እንዲሰጡ ጠየቀ፡፡ ሰዎች እንዲሠሩ ለመገፋፋት ስለ ሥራው በስሜት ተናገረ፡፡

2/ አስቀድሞ እቅድ እንዳላወጣ፣ ግልጽ መመሪያ እንዳልሰጠ አስፈላጊውን ነገር እንዳላሟላ ማስተዋል ይኖርብሃል፡፡

3/ መ/ ጌታ እንደሚጠቀምበት እምነት ነበረው፡፡

4/ ሀ/ ያለበትን ደረጃ በሀቅ አስደግፎ ተናገረ፡፡

5/ ለ/ ሥልጠናና ብቃት

6/ የአንተ መልስ

7/ ሀ/ 3/ሰዎች ለ/5/ቁሳቁሶች ሐ/6/ዓላማዎች መ/1/ጊዜ ሠ/4/ ዘዴዎች ረ/2/ሥፍራ 8/ሐ/ የሥራውን ሂደት ለመወሰን የምናደርገው 6/የአንተ መልስ ሙከራ እቅድ

9/ በመንፈሳዊ ሥራ ውስጥ ሊገጥሙን የሚችሉ ሦስት መሰናክሎች፡-

1/ እቅዶች ሁልጊዜ ተፈጻሚ አይሆኑም

2/ እቅድ ስለሚያወጡ ክርስቲያኖችን ሰዎች ሊወቅሷቸው

3/ እቅድ ጊዜንና በርትቶ መሥራትን ይጠይቃል፡፡

10/ ሐ/ በመዋቅሩ ውስጥ ያለውን ሥፍራ ማወቅና አስፈላጊ ሰዎችን ማደራጀት